

# የኢየሱስ ትምህርቶች

ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ሲሰብክ ለማየት ወደእርሱ ይሰበሰቡ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ተአምራትን ይፈፅም ነበር። ሰዎቹም እርሱ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ያውቁ ነበር።. እርሱም ብዙ ነገሮችን ያስተምራቸው ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ከገሊላ ባህር ዳርቻ አጠገብ ባለው ተራራ ላይ አስተማረ። እርሱም እግዚአብሔርን እያስደሰቱ እንዴት መኖር እንዳለባቸው አስተማራቸው።

አስታራቂዎች እንዲሆኑ አስተማራቸው። እንዲህ ካደረጉም የእግዚአብሔር ልጆች እንደሚባሉ ነገራቸው።

ጠላቶቻቸውን እንዲወዱና ለሚጠሏቸው ሰዎች መልካምን እንዲያደርጉ አስተማራቸው። ስለሚያሳድዷቸው ሰዎችም እንዲፀልዩ አስተማራቸው።

በተጨማሪም እንደጨው፣ በተራራ ላይ እንዳለች ከተማና በመንገድ ሌሎች እንደሚያበራ መብራት እንዲሆኑ አስተማራቸው። ተከታዮቹ ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ በመሆን መልካሙን እንዲያደርጉ እንዲያስተምሯቸው አዘዛቸው።

ኢየሱስ ካለን ሌሎች ሰዎች ማካፈል  እንዳለብን አስተማረ።

" በሌሎች ላይ መፍረድ እንደማይገባንና በማንኛውም ነገር መጨነቅ እንደሌለብን፣ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር እንደሚያስብልን አስተማረ።

*.እነኝህ ትምህርቶች የሚገኙት በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 5 እና 6 ነው።*

http://gardenofpraise.com